**የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በኮሎኝ**
Komitee zur Unterstützung der EPRP in Köln
Postfach 100110, 40441 Köln, Deutschland

ጥር 5 ቀን 1999 አ.ም.
13. January 2007 አ.ም.

# የወይዘሮ አዜብ ጎላ ሽልማትን እናወግዛለን

እኛ በኮሎኝ ከተማ በጀርመን ሀገር የምንገኝ የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ አባላት፤ የአቶ መለስ ዜናዊ ባለቤት ወይዘሮ አዜብ ጎላህ በአሜሪካን አገር በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ቀሳፊውንና የብዙ ዜጎቻችንን ሕይወት አጥፊ የሆነ የኤዲስ በሽታን በመከላከል ረገድ ባደረገችው „መልካም ተግባር" በሚል የክብር ሽልማትና እውቅና ለመስጠት መወሰኑን ሰምተናል። አውቀናል። ይህ የተባለው „ሽልማትና ዕውቅና" „መልካም አርአያነት" በሌለበት የሚሰጥ ዳረጎት በመሆኑ እኛን ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን በያለንበትና በምንኖርበት አህጉር ሁሉ በእጅጉ ያሳዘነን፤ ያስቆጣንና ያስደነገጠን ጉዳይ መሆኑን፤ ብሎም በዚህች ሴትና እንዲሁም አምነውና ተግባሬና ተልዕኮዬ ብለው ለጸረ ኢትዮጵያ ሕዝብ ባቋቋሙት ድርጅት ማለትም ሕወሀት ሆነ ኢሕአደግ አማካኝነት፤ ከጨካው ሕይወታቸው ጀምሮ እስከ በትረ ሥልጣናቸው ጉዞ ድረስ በቅንጅትና ተባባሪነት ያደረጉትን እኩይ ተግባርና ታሪክ ለመሸፈን የሚደረግ ደባ ሆኖ እንድንመለክት የሚያስገድደን ሆኖ አግኝተነዋል።

ወይዘሮ አዜብና አቶ መለስ በዚህም ተባለ በዚያ በባሕሪያቸውም ሆነ በተግባራቸው ከባለቤታቸው የማይለዩ፤ በሌላ አነጋገር ከአንድ እንጨት/ዛፍ የተጠረቡ፤ በአንድ ድርጅትና አላማ የታቀፉ፤ በአንድ ሳምባ የሚተነፍሱ ለመሆናቸው ለእኛም ሆነ ለእነርሱ ለባለ ጉዳዮቹ ግልጽ የሆነ ነው ብለን እናምናለን።

ከ17 አመታት ጀምሮ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፋፍለው እያፋጁ ያሉና እያዋረዱት ያሉ ሁለት እርግማንና የአንድ ሳንቲም ግልባጭ እንደሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፤ ሰብአዊ ፍጡርነት ያለው የሰው ልጅ ጉዳይ በመሰረቱ ያገባኛል የሚል ብሎም ኢትዮጵያን እንደ ኢትዮጵያዊነቷ የሚያውቋት ሁሉ ጥሩ አድርገው ያውቋቸዋል ብለን አጥብቀን እናምናለን።

ይህም በመሆኑ ይህ የጆርጂያ ታውን ዩኒቨርሲቲ የማርቲን ሉተር ተቋም፤ ለዚህች ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ዴሞክራቲክ ወንጀለኛ ተጋዳሊት፤ ከባለቤቷና ከርሱ አገዛዝ ነጥሎ ለማየት መሞከር፤ ለመብታቸው ሲሉ ለታገሉ፤ ለማንነታቸው ሲሉ ለተጋደሉ፤ ለሀገር ነጻነትና ለሕዝባችን ተከባብሮ በእኩልነት አብሮ መኖር ሲሉ የተሰዉትን፤ የታሰሩትንና ደብዛቸው የጠፉትን እንዲሁም ከሚወዷት ሀገር ተባርረውና ተሰደው የሚገኙትን የዜጎቻችንን ሕይወት፤ የጀግነንት ተግባር ማርከስና ማዋረድ ነው ብለን እናምናለን።

ይህችን ወይዘሮ አዜብ መስፍን/ጎላን ስናነሳ ከቶውንም ቢሆን የማናልፋቸው አንዳንድ ክስተቶችን እንገነዘባለን። በተለይም ከግንቦቱ ምርጫ ጋር ተያይዞ በእርግዝናዋ ወቅት

በእሥር ቤት ስለነበረችው ጋዜጠኛ ወይዘሮ ፍሬዘር ነጋሽ፤ ዛሬም በእሥር ቤት ፍዳዋን ስለምታየው ወይዘሮ ሰርቃለም ፋሲልና ሌሎችንም በተመሳሳይ ደረጃ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ እሥር ቤቶች ለሚሰቃዩ፤ መብታቸው እንዲከበር ለታገሉ ሴቶቻችንን ምንም አይነት ርህራሄና እንዲፈቱ ጥረት ስታደርግ ያልተደመጠች መሆኗን መጥቀሱ ብቻ ይበቃል። እኛ በበኩላችን ግን እነዚህን እህቶቻችንን እናስታውሳለን እንዘክራለንም። ብዙ ነገሮች ማንሳት እንችላለን። ይህ ግን የጠቀስነው የተለየ መሆኑን ለማንሳት ብቻ ነው። ጥያቄያችንና መልዕክታችን ይህች የገዢው ፓርቲ የሕወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆነች ተጋዳሊት ሴት፤ በሷና በባሏ ሥም በውጭ ሀገር ባንኮች በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያሸሸች፤ ለጸረ ኤድስ መከላከያ በሚል ሽፋን ገንዘብ ለማካበቻ ተጠቃሚ የሆነች ተብላ በሙስና ወንጀል የምትታማ፤ ከባሏ የተለየ ምን በጎ ነገር በሕይወቷ ለኢትዮጵያ ሰርታለች የሚለውን ለማሳየት ያህል እንጂ?!

ታዲያ የዚህ የማርቲን ሉተር ተቋም አንድ ልብ ሊለው የሚገባው ነገር ቢኖር፤ በዚህች ጸረ ኢትዮጵያ ሕዝብና ወንጀለኛ ሴት ሥምና ምክንያት የተነሳ የታላቁን የጥቁር ሕዝብ አርአያና ተሟጋች ሥም እንዳያዋርድ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብና ለመብቱ፤ ለማንነቱና ለሰብአዊ መብቱ ብሎም ለአንድነቱ የሚያደርገውን ትግልና አላማ እንዲሁም ታሪክ እንዳያንቋሽሽ እናሳስባለን። እናስገነዝባለን። ይህ ሆኖ ባይገኝ ተቋሙና ዩኒቨርሲቲው እንዲሁም ሽላሚዎቹና ሿሚዎቹ በመለስ አገዛዝ አማካኝነት በሕዝባችን ላይ ላለፉትና አሁንም እየፈጸሙ ያሉትን የበደልና የጥፋት ድርጊቶች እውቅና መስጠና ለወደፊቱም በዚሁ ድርጊቶቻቸው እንዲቀጥሉ ማበረታት ስለሆነ በታሪክ ሀላፊነት፤ በአጥፊነትና በአስጸያፊነት የሚወቀሱ፤ የሚጠየቁና የሚታሰቡ መሆናቸው ግልጽ እንዲሆንላቸው እናስገነዝባለን። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ይህ ድርጊት  ያንን የሰው ልጅ ታሪክ ባለውለታና ክቡር ሰው የሆነውን የማርቲን ሉተር ኪንግ ቀዳማዊ ታሪክ አጉዳፊና አርካሽ ድርጊት ነው ብለን እናምናለን፤ እናስገነዝባለን።

በመጨረሻም „ሽልማቱንና ዕውቅናውን“ በተመለከተ እኛ እንደ ኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በኮሎኝ/ጀርመን ያለን አማራጭ ቢሆን በኢትዮጵያችን ወንጀለኛና ግፈኞችን፤ ሕዝብን አዋራጅና አፋኞችን፤ እንዲሁም ገዳዮችን ሳይሆን ማሞገስ የሚገባው፤ ለበጎ አላማና ለወገኖቻችን፤ አብሮ መኖር፤ ለታሪካችንና ለተከበረው ሕዝባችን እንዲሁም ለክቡር አላማው ክቡር ሕይወታቸውን በኩራት፤ በጽናትና በደስታ ለመስዋዕትነት እነሆን ያሉትን ብዙ እጅግ ብዙ ሰማዕታት እንደነበሩን፤ እንዳሉን ወደፊትም እንደሚኖሩን በአጽንዖት መግለጽ እንወዳለን። እነዚህ ዜጎቻችን ተግባሮቻቸው ከሕዝባችን ባሻገር በአለም አቀፉ ማህበረሰብ እውቅና አግኝተው ቢሸለሙ እቅፍ አበባ በማቅረብና ከልብ በሚመነጭም ፈገግታ በማጀብ ከሁሉም በላይ ደስተኞች እኛው ኢትዮጵያዊያኖች መሆናችን ደግሞ ሊታወቅልን ይገባል እንላለን።

*ግፈኛና ወንጀለኛ መሸለምና መሸፋፈን ያብቃ !!*
*ወ/ሮ አዜብ እንደባሏ ለፍርድ ትቅረብ!!*
*እውነትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ታግሎ ያቸንፋል!!*

በኮሎኝ የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ